# የምርት ገበያ የማገዘን ወኪሎች የአሠራርና የቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 543/2013ን እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 774/2013

የምርት ገበያ የማጋዘን ወኪሎች የአሠራርና የቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 543/2013ን /እንደተሻሻለው/ እንደገና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 551/1999 /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አወጥቷል፡፡

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የምርት ገበያ የማጋዘን ወኪሎች የአሠራርና የቁጥጥር መመሪያ /ማሻሻያ/ ቁጥር 774 /2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ማሻሻያ**

የምርት ገበያ የማጋዘን ወኪሎች የአሠራርና የቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 543/2013 /እንደተሻሻለው/ እንደገና እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1. የመመሪያው አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (7) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (7) ተተክቷል፡፡

"(7) **'ተገበያይ አባል'** ማለት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚጠየቀውን የመመዘኛ መሥፈርት በማሟላት በባለሥልጣኑ ዕውቅና በማግኘት በአባልነት ተመዝግቦ ለራሱ ብቻ ምርት በመግዛት ወይም በመሸጥ ግብይት የሚፈፅም ሰው ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃጸም አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይንም ይጨምራል፡፡"

2. የመመሪያው አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (3) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) ተተክቷል፡፡

"(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በወካዩ የሚሰጥ ወክልና በጊዜ ገደብ ተወስኖ ካልተሰጠ ወይም በወካዩ የወክልና መሻሪያ ካልቀረበ ወይም ተወካዩ የወክልናው ኦሪጅናል ቅጅ በእጁ ላይ ከሌለ በስተቀር አንድ ጊዜ የተደረገው የተወካዩ ምዝገባ እንደጸና ይቆያል፡፡"

3. ከመመሪያው አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (1) (ረ) ቀጥሎ የሚከተሉት ከ(ሰ) እስከ (ቸ) ተጨምረዋል፡፡ የቀድሞው አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሰ) (ኀ) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

''(ሰ) የማጋዘን ወኪልነቱ ለሻጭ ከሆነ በምርት ገበያው ምርቱን ለማስረከብ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች ተሟልተው ከምርቱ ጋር መቅረባቸውን የሚረጋገጥ እና የተጓደሉ ሰነዶች እንዲሟሉ የሚድረግ፣

(ሸ) ናሙና በሚወሰድበት ጊዜ የሚዛ ክፍያ የሚፈፀም እና ለተፈፀመው ክፍያ ለወካዩ ደረሰኝ የሚቅረብ፣

(ቀ) ምርት የጫኝ ተሽከርካሪ ምዝና በሚያካሂድበት ጊዜ ጭነቱን የማስመዝን፣"

(በ) የማጋዘን ወኪልነቱ ለገዥ ከሆነ የርክክብ ሰነዶች ተሟልተው መቅረባቸውን የሚረጋገጥ እና የጭነት ተሽከርካሪዎች አግባብነት ባለው ማስሪያ ቤት በቅርንጫፉ በተመደበ ባለሙያ ታሽገውና ማሸኛ ሰነድ ይዘው መውጣታቸውን የሚረጋገጥ፣

(ተ) በምርት ገበያው ላይ ምርትን ለማስረከብም ሆነ ለመረከብ አስፈላጊ ስለሆኑ ማስፈርቶች እና ሰነዶች ለወካዩ ግንዛቤ የመፍጠር፣

(ቸ) የምርት ርክክብን በተማለከተ የሚለጠፉ ማንኛውንም የምርት ገበያ ማስታወቂያዎች ለወካዩ በወቅቱ የማሳወቅ፣''

4. የመመሪያው አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (4) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (4)ተተክቷል፡፡

"(4) የባለሥልጣኑን ዕወቅና አግኝቶ በመሥራት ላይ ያለ የመድረክ/የግብይት ወኪል በወካዩ ተሞልቶ የተፈረመውን የወክልና ቅፅ እና ባለሥልጣኑ የሰጠውን የመድረክ/የግብይት ወኪልነት የዕወቅና የምስክር ወረቀት በማቅረብ እንዲሁም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 መሠረት የተማለከቱትን የመመዝገብና መዝገብ የመያዝ ግዴታዎች በማሟላት የምርት ገበያውን አባል ወይም አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይን በመወከል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተማለከቱትን የማጋዘን ተግባራት ሊያከናውን ይችላል፡፡"

5. ከመመሪያው አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (6) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (7) ተጨምሯል፡፡

"(7) በሌላ ሕግ በግልፅ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም የማጋዘን ወኪል፣ የማጋዘን ወኪልነትን ደርቦ የሚሠራ የመድረክ/የግብይት ወኪል ወይም የቤተሰብ ወኪል ተወክሎ መሥራት የሚችለው በሻጭ/በምርት አስረካቢ ወይም በገዥ/በምርት ተረካቢ ወገን በኩል ብቻ በመሆን ነው፡፡"

6. የመመሪያው አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ) **እና** (መ) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (ሐ) **እና** (መ) ተተክተዋል፡፡

"(ሐ) ወካዩ በወክልና ማስጫ ሰነዱ ላይ ግልፅ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር ወክልና የተቀበለበትን ሥራ ለሌላ ሦሥተኛ ሰው በወክልና በማስጠት የማያሠራ መሆኑን፣ የወካዩ ግልፅ ፈቃድ በተሰጠው ጊዜም የሚወክለው ሦሥተኛ ሰው እርሱ በሚሠራበት የምርት ማከማቻ መጋዘን ብቻ የሚሠራና በሁለቱም ተወካዮች የሚስተናገደው የተሽከርካሪ ጭነት ማጠን በዚህ መመሪያ ከተቀማጠው የቀን እና የዓመት ገደብ በላይ የማይሆን መሆኑን፣

(መ) ወኪሉ የኅብረት ሥራ ማኅበር፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ኅብረት፣ የቤተሰብ ወኪል ወይም ምርት ተረካቢ ወኪል ካልሆነ በስተቀር የተቀበላቸው ወክልናዎች በሙሉ በአንድ የምርት ማከማቻ መጋዘን ብቻ የተወሰኑ መሆኑናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም በምርት ማከማቻ መጋዘን መሙላት ወይም በሌላ አስገዳጅ ምክንያት የምርት ገበያው ምርቱን ወደ ሌላ መጋዘን ካዛወረው የምርት ገበያው የሚሰጠውን የሚረጋገጫ ደብዳቤ በማቅረብ ለተዛወረው ምርት ብቻ ምርቱ በተዛወረበት መጋዘን የወክልና ተግባሩን ሊያከናውን ይችላል፡፡"

7. የመመሪያው አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (4) **እና** (5) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (4) **እና** (5) ተተክተዋል፡፡

"(4) ስለመዝገብ አያያዙም ሆነ ስላከናወነው ሥራ በምርት ገበያው **እና/ወይም በ**ባለሥልጣኑ የሚመለከተው የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ሲጠየቅ የማሳየትና አስፈላጊውን መረጃ የማስጠት ግዴታ አለበት፡፡

(5) ወኪሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚያደራጀውን መዝገብ ቢያንስ ለሦሥት ዓመታት ጠብቆ ማቆየት አለበት፡፡"

8. የመሚያው አንቀጽ11 ርዕስ **እና** የመጀመሪያው አረፍተ ነገር እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"**11.** የማዘን ተግባራትን በራሳቸው ስለሚያከናወኑ አቅራቢዎች እና ገዥዎች

የማዘን ተግባራትን በራሱ የሚያከናወን አቅራቢ ወይም ገዥ፣ በዚህ መሚያ ወስጥ የተማለከቱትን ሌሎች ድንጋጌዎች ማክበር ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ 7 የተማለከቱትን ተግባራት ሲያከናወን፡-"

9. የመሚያው አንቀጽ 17 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 17 ተተክቷል፡፡

**"17. የማዘን ወኪሎች የሥነ ምግባርና ቁጥጥር ኮሚቴ ስለማቋቋም**

(1) በማዘን ወኪሎች ላይ የሚቀርበወን የዲሲፕሊን ክስ መርምሮ ወሳኔ የሚሰጥ አምስት አባላት የሚኖሩት የማዘን ወኪሎች የሥነ ምግባርና የቁጥጥር ኮሚቴ በእያንዳንዱ የምርት ገበያ የምርት ማከሚቻ ማዘን ይቋቋማል፡፡

(2) ኮሚቴወም የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

(ሀ) የምርት ማከሚቻ ማዘኑ ኃላፊ ....ሰብሳቢ

(ለ) የማዘኑ የአስተዳደር ሠራተኛ ወይም የአስተዳደር ሠራተኛ በሌለበት ማዘን የምርት ማከሚቻ ማዘኑ ኃላፊ የሚመድበው ሠራተኛ ...ም/ሰብሳቢ

(ሐ) በምርት ማከሚቻ ማዘኑ በሻጭ/በአስረካቢ ወገን የሚሠሩ የማዘን ወኪሎች ተወካይ ......አባል

(መ) በምርት ማከሚቻ ማዘኑ በገዢ/በተረካቢ ወገን የሚሠሩ የማዘን ወኪሎች ተወካይ.......አባል

(ሠ) በምርት ማከሚቻ ማዘኑ ኃላፊ የሚመደብ ሠራተኛ........... ...............አባልና ፀሐፊ፡፡

(3) የኮሚቴው ስብሰባ በሰብሳቢው ወይም እርሱ በሚይገኝበት ጊዜ በምክትል ሰብሳቢው ሊጠራና ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

(4) በእያንዳንዱ የዲሲፕሊን ክስ የመጀመሪያ ስብሰባ ሰብሳቢወን ወይም እርሱ በሚይገኝበት ጊዜ ም/ሰብሳቢወን እና በሻጭ/በአስረካቢ ወገን የተመረጠወን የማዘን ወኪሎች ተወካይ ወይም በገዢ/በተረካቢ ወገን የተመረጠወን የማዘን ወኪሎች ተወካይ ጨምሮ ሦሥት የኮሚቴው አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል፡፡ ሆኖም በመጀመሪያው ስብሰባ ምልዐተ ጉባዔው ካልተሟላ በቀጣዮቹ ስብሰባዎች ሰብሳቢወን ወይም እርሱ በሚይገኝበት ጊዜ ም/ሰብሳቢወን ጨምሮ ሦሥት የኮሚቴው አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

5) ኮሚቴው ወሳኔ የሚሰጠው በድምፅ ብልጫ ሲሆን ድምፅ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ ግን በሰብሳቢው ወይም ሰብሳቢው በሌለ ጊዜ በምክትል ሰብሳቢው ድጋፍ ያገኘው ሃሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

(6) የሻጭ/የአስረካቢ ወገን የማዘን ወኪሎች ተወካይ በማዘኑ በሚሠሩ የሻጭ/የአስረካቢ ወገን ወኪሎች ጠቅላላ ስብሰባ በቀጥታ ይመረጣል፡፡ እንዲሁም የገዢ/የተረካቢ ወገን የማዘን ወኪሎች ተወካይ በማዘኑ በሚሠሩ የገዢ/የተረካቢ ወገን ወኪሎች ጠቅላላ ስብሰባ በቀጥታ ይመረጣል፡፡

(7) የኮሚቴው አባል የዲሲፕሊን ክስ ከቀረበበት የማዘን ወኪል ጋር የወክልና፣ የንግድ ግንኙነት፣ ፀብ፣ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው እንደሆነ በራሱ ወይም በሌሎች ሰዎች ጥያቄ ሲቀርብ ጉዳዩን ማየት የለበትም፡፡ እንዲሁም የኮሚቴው አባል የዲሲፕሊን ክስ ሲቀርብበት ወይም በማናቸውም ምክንያት ሥራወን ሲለቅ አባሉን የወከለው አካል በምትኩ ሌላ ተወካይ መተካት አለበት፡፡

(8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(2) (ሐ) እና (መ) የተማለከቱት ተወካዮች የአገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ነው፡፡ ሆኖም ለቀጣይ የአገልግሎት ዘመን በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፡፡"

10. የመሚያው አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ (1) **እና** (2) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (1)

**እና** (2) ተተክተዋል፡፡

"(1) ኮሚቴው በሰጠው ወሳኔ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ወሳኔው በተሰጠው በ30 ቀናት ወስጥ ከፈለገ በምርት ገበያው በአካል በማኘት ወይም በምርት ማከማቻ መጋዘኑ ኃላፊ በኩል የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ይግባኙን ለምርት ገበያው የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፡፡

(2) የምርት ገበያው የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴ በመጋዘን ወኪሎች የሥነ ምግባርና የቁጥጥር ኮሚቴ የተሰጠወን ወሳኔ መርምሮ ሊያጸናው፣ ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው ይችላል፡፡ የግብይት አፈጻጸም ኮሚቴው ቅሬታውን ሲመረምር እንደነገሩ ሁኔታ ተከራካሪ ወገኖችን በአካል በማስቀረብ ወይም የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ማነጋገር ይችላል፡፡ የሚሰጠወን ወሳኔም በምርት ማከማቻ መጋዘኑ ኃላፊ በኩል በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡"

11. ከመመሪያው አንቀጽ 26 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 27 ተጨምሯል፡፡ የቀድሞዎቹ አንቀጽ 27፣ 28 እና 29 እንደቅደም ተከተላቸው አንቀጽ 28፣ 29 እና 30 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

"27. **ሪፖርት ስለማቅረብ**

እያንዳንዱ የባለሥልጣኑ የማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት በሚከታተላቸው የምርት ማከማቻ መጋዘኖች የሚሠሩ የመጋዘን ወኪሎችን በተመለከተ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ዝርዝር ጉዳዮች የያዘ ሪፖርት በማጠናቀር በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት፣ የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት፣ የዘጠኝ ወርና ዓመታዊ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት ማቅረብ አለበት፡-

(1) የመጋዘን ወኪሎችን ብዛት እና የወከሏቸወን ወካዮች ብዛት፣

(2) በሻጭ/በአስረካቢ ወገን ተወክለው የሚሠሩ የመጋዘን ወኪሎችን ብዛት እና የወከሏቸወን ወካዮች ብዛት፣

(3) በገዢ/በተረካቢ ወገን ተወክለው የሚሠሩ የመጋዘን ወኪሎችን ብዛት እና የወከሏቸወን ወካዮች ብዛት፣

(4) በመድረክ/በግብይት ወኪልነት ላይ የመጋዘን ወኪልነትን ደርበው የሚሠሩ የመጋዘን ወኪሎችን ብዛት እና የወከሏቸወን ወካዮች ብዛት፣

(5) የቤተሰብ የመጋዘን ወኪሎችን ብዛት እና የወከሏቸወን ወካዮች ብዛት፣

(6) ከዚህ በላይ ከንዑስ አንቀጽ (2) እስከ ንዑስ አንቀጽ (5) የተመለከቱት ተወካዮች በየምድባቸው ያስተናገዱትን የጭነት ተሽከርካሪዎች ብዛት፣

(7) በአንድ ተወካይ የተስተናገደወን ዝቅተኛና ከፍተኛ የወካዮች ብዛት፣

(8) በአንድ ተወካይ የተስተናገደወን ዝቅተኛና ከፍተኛ የጭነት ተሽከርካሪዎች ብዛት፣

(9) የመጋዘን ወኪሎችን በተመለከተ የቀረቡ ቅሬታዎችን ብዛት፣

(10) የዲሲፕሊን ክስ የቀረበባቸወን የመጋዘን ወኪሎች ብዛት፣

(11) ከቀረበባቸው የዲሲፕሊን ክስ በነፃ የተሰናበቱትን የመጋዘን ወኪሎች ብዛት፣

(12) በቀረበባቸው የዲሲፕሊን ክስ ጥፋተኛ ሆነው የተቀጡትን የመጋዘን ወኪሎች ብዛት፣

(13) በቀረበባቸው የዲሲፕሊን ክስ ጥፋተኛ ሆነው በወክልናቸው እንዳይሠሩ የተወሰነባቸወን የመጋዘን ወኪሎች ብዛት፣

(14) በቀረበባቸው የዲሲፕሊን ክስ ጥፋተኛ ሆነው የተቀጡ የመጋዘን ወኪሎች የፈፀሟቸወን የሕግ ጥሰቶች ዝርዝር፣

(15) የማስተባበሪያ ፅህፈት ቤቱ የሚያቀርባቸው ተጨማሪ አስተያየቶች (ካሉ)፡፡"

12. አንቀጽ 28 ሆኖ በተሸጋሸገው የመመሪያው አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (2) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) ተጨምረዋል፡፡

"(3) በሻጭ/በአስረካቢ እና በገዥ/በተረካቢ ወገን በኩል ተወክሎ በመሥራት ላይ የሚገኝ የመጋዘን ወኪልነትን ደርቦ የሚሠራ የምርት ገበያ አባል የመድረክ/የግብይት ወኪል፣ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ወኪል፣ የቤተሰብ ወኪል ወይም ሌላ ማንኛውም የመጋዘን ወኪል ይህ መመሪያ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለወካዮቹ አስቀድሞ በማሳወቅ ወክልናውን በሻጭ/በአስረካቢ ወይም በገዥ/በተረካቢ ወገን በኩል ብቻ አድርጎ ማስተካከል አለበት፡፡ ይህ መመሪያ ከፀናበት ቀን ጀምሮ ከሦስት ወራት በኋላ ማንኛውም የመጋዘን ወኪል በሻጭ/በአስረካቢ እና በገዥ/በተረካቢ ወገን በኩል ሆኖ መሥራት አይችልም፡፡

(4) የመጋዘን ወኪልነትን ደርቦ የሚሰራ የምርት ገበያው አባል የመድረክ/የግብይት ወኪል፣ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ወኪል እና የቤተሰብ ወኪል ይህመመሪያ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ በመመሪያው አንቀጽ 4መሠረት የመመዝገብና መዝገብ የመያዝ ግዴታዎችን በማሟላት መሥራት አለበት፡፡ ይህመመሪያ ከፀናበት ቀን ጀምሮ ከሦስት ወራት በኋላ የመመዝገብና መዝገብ የመያዝ ግዴታዎችን ያላሟላ ማንኛውም የመጋዘን ወኪልነትን ደርቦ የሚሰራ የምርት ገበያው አባል የመድረክ/የግብይት ወኪል፣ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ወኪል እና የቤተሰብ ወኪል በወክልናው መሥራት አይችልም፡፡"

## 3. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ቦርድ ከፀደቀበት ከዛሬ ጥቅምት 6 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን ቦርድ
ጥቅምት 6 ቀን 2013 ዓ.ም
አዲስ አበባ